የመጀመሪያ ረቂቅ

ደንብ ቁጥር _____

ስለኢንቨስትመንት ማበረታቻ የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

በገቢ ግብር አዋጅ (እንደተሻሻለ) ቁጥር 979/2008 አንቀጽ 105 በኢንቨስትመንት ሕጉ መሰረት ኢንቨስትመንት ፈቃድ የተሰጣቸው ኢንቨስተሮች ሊሰጣቸው የሚገባው የገቢ ግብር ማበረታቻ የሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚያወጣው ደንብ ሊወሰን እንደሚገባ የተደነገገ በመሆኑ፤

የኢንቨስትመንት ማበረታቻ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ (እንደተሻሻለ) ቁጥር 517/ 2014 አንቀጽ 7 የሚኒስትሮች ምክር ቤት በደንቡ የተቋቋመውን የገቢ ግብር የማበረታቻ ዓይነት በሌላ የማበረታቻ አይነት ሊተካው እንዲሚችል የሚደነግግ በመሆኑ፤

በስራ ላይ ያለው የኢንቨስትመንት ማበረታቻ በውጤት ላይ ያልተመሰረተ ስለሆነ፤ ለኢኮኖሚው እድገት አስተዋጽኦ ላላቸው ከፍተኛ ካፒታል ለሚጠይቁ የኢንቨስትመንት መስኮች የተለየ ትኩረት በማይሰጥ ሁኔታ ማበረታቻ እየተፈቀደ ኢንቨስትመንትን በሚፈለገው ደረጃ ማበረታታት ስይቻል በመቆየቱ፤

ይህንን ሁኔታ በመቀየር ቅድሚያ በሚሰጣቸው የኢንቨስትመንት መስኮች ላይ ያተኮረ፤ በስራ ላይ የሚውለውን ካፒታል ከግምት ውስጥ የሚያስገባ እና በውጤት ላይ የተመሰረተ የኢንቨስትመንት ማበረታቻ ስርአት ስራ ላይ ማዋል አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

ማበረታቻዎችን በተመለከተ ተጠያቂነትን ለማጎልበት፣ ከዓለም አቀፍ ተለዋዋጭ ሁኔታዎች ጋር እንዲጣጣም ለማድረግ እና የሚሰጡት ማበረታቻዎች ቀላል እና ግልፅ እንዲሆኑ ማድረግ አስፈላጊ በመሆኑ፤

የሚኒስትሮች ምክር ቤት በኢንቨስትመንት አዋጅ ቁጥር 1180/2012 አንቀፅ 17 እና በጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/2006 (እንደተሻሻለ) አንቀጽ 129(6) መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

ክፍል አንድ

ጠቅላላ ድንጋጌዎች

1. አጭር ርዕስ

ይህ ደንብ “የኢንቨስትመንት ማበረታቻ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር /2018” ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

CamScanner

2. ትርጓሜ

በአዋጁ ለቃላት እና ሀረጎች የተሰጠው ትርጉም እንደተጠበቀ ሆኖ በዚህ ደንብ ውስጥ፡

-

1) **“የኢንቨስትመንት ማበረታቻ”** ማለት በዚህ ደንብ መሰረት ለማበረታቻ ብቁ ለሆነ ኢንቨስትመንት በዚህ ደንብ አንቀጽ 6 የተዘረዘሩት ማበረታቻዎች ናቸው፡፡

2) “**የኢንቨስትመንት ካፒታል አላዋንስ**” ማለት አንድ ኢንቨስትመንት ስራ በሚጀምርበት ወቅት ለካፒታል ንብረቶች ባወጣው ወጪ ላይ በተወሰነ መቶኛ የሚሰላ ለአንድ ጊዜ ብቻ የሚፈቀድ ተቀናሽ ወጪ ነው፡፡

3) **”የአፈጻጸም ስምምነት”** ማለት በባለሀብቱ እና አግባብ ባለው የኢንቨስትመንት ባለስልጣን መካከል በዚህ ደንብ አንቀጽ 25 በተመለከተው መሰረት የሚደረግ ውል ነው፡፡

4) **“ተቀባይነት ያለው ወጪ”** ማለት ለካፒታል ዕቃዎች ማፍሪያ የዋለ እና ሚኒስቴሩ በሚያወጣው መመሪያ የተመለከቱትን መስፈርቶች የሚያሟላ ወጪ ነው፡፡

5) **“አዋጅ”** ማለት የኢንቨስትመንት አዋጅ ቁጥር 1180/2012 ነው፡፡

6) **“ካፒታል”** ማለት የአገር ውስጥ ወይም የውጭ ገንዘብ፣ የሚተላለፍ ሰነድ፣ የማምረቻ ወይም የአገልግሎት መስጫ መሳሪያ፣ ህንጻ፣ የሥራ ማስኬጃ ካፒታል፣ የንብረት መብት፣ የአእምሯዊ ንብረት መብት ወይም ሌላ የሚዳሰስ ወይም የማይዳሰስ የንግድ ሀብት ነው፤

7) **“የካፒታል ዕቃ”** ማለት ለሽያጭ የሚውሉ ምርቶችን ለማምረት ወይም አገልግሎቶችን ለመስጠት ጥቅም ላይ የሚውል፣ ከአንድ ዓመት ላላነሰ ጊዜ ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ያለው መሣሪያን እና እነዚህን የመሳሰሉ ግዙፋዊ ሀልዎት ያላቸውን ሌሎች ንብረቶች ይጨምራል::

8) “**ማምረት**” ማለት በኢትዮጵያ ውስጥ የኢንዱስትሪ ሂደትን በመጠቀም ጥሬ ዕቃ ወይም ግብአት በምርት ሂደት ውስጥ በማሳለፍ፤ በማቀናበር ወይም ቅርጹን ወይም አገልግሎቱን በመለወጥ ሌላ አዲስ መጠሪያ ወይም ባህሪ እና ጠቀሜታ ያለው እቃ ማውጣት ሲሆን ሚኒስቴሩ በሚያወጣው መመሪያ የሚወስናቸውን ሙሉ ለሙሉ ተበታትነው ወደ አገር የሚገቡ ዕቃዎችን መገጣጠም ሊጨምር ይችላል፡፡

9) **“የግንባታ ዕቃ”** ማለት የህንጻ ወይም የግንባታ ስራ አካል የሚሆን ለግንባታ ሥራ የሚውል ዕቃ ነው፡፡

10) **“ልዩ የኢኮኖሚ ዞን”፤ “የልዩ የኤኮኖሚ ዞን አልሚ”፤ “የልዩ የኤኮኖሚ ዞን ንኡስ አልሚ”፤ እና የልዩ የኤኮኖሚ ዞን ድርጅት”** የሚሉት ሃረጎች በልዩ የኤኮኖሚ ዞን አዋጅ ቁጥር 1323/2016 የተሰጣቸውን ትርጉም ይይዛሉ፡፡

11) **“ስታርታፕ”** እና **““የስታርታፕ ምጎዳር ገንቢ”** የሚሉት ቃላት በስታርታፕ አዋጅ ቁጥር 1396/2017 የተሰጣቸውን ትርጉም ይይዛሉ፡፡

CamScanner

12) **“ተቆጣጣሪ መስሪያ ቤት”** ማለት የኢንቨስትመንት ተቋማት፣ የማዕድን ሚኒስቴር፣ የማዕድን ቢሮዎች፣ የንግድና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስቴር፣ የታክስ ባለስልጣን፣ የጉምሩክ ኮሚሽን እና ሌሎች የኢንቨስትመንት ማበረታቻ አፈፃፀምን ለመቆጣጠር በሕግ ስልጣን የተሰጣቸው አካላት ናቸው፡፡

13) **“የኢንቨስትመንት ተቋም”** ማለት የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን ወይም የክልል መንግሥታት እንዲሁም የድሬዳዋ እና የአዲስ አበባ ከተማ መስተዳድሮች የኢንቨስትመንት መስሪያ ቤቶች ናቸው፡፡

14) **“የታክስ ባለስልጣን”** ማለት የገቢዎች ሚኒስቴር ወይም የክልል መንግሥታት እንዲሁም የድሬዳዋ እና የአዲስ አበባ ከተማ መስተዳድሮች የገቢዎች ቢሮዎች ናቸው፡

15) **“የገቢ ግብር”** ማለት በፌዴራል ወይም በክልል መንግሥታት የገቢ ግብር አዋጆች በሠንጠረዥ “ሐ” በተመለከተው ገቢ ላይ የተጣለ ግብር ነው፡፡

16) **“የጉምሩክ ቀረጥ እና ታክስ ማበረታቻ”** ማለት ባለሀብቱ ለኢንቨስትመንቱ አስፈላጊ የሆኑትን የካፒታል ዕቃዎች፣ የግንባታ ዕቃዎች እና ተሽከርካሪዎችን ሚኒስቴሩ በሚያወጣው መመሪያ በሚወስነው መሰረት ከቀረጥና ታክስ ነፃ በመሆን ወይም በአነስተኛ መጣኔ የቀረጥና ታክስ በመክፈል ወደ አገር የሚያስገባበት ሥርዓት ነው፡፡

17) **“ቀረጥ”** በጉምሩክ አዋጅ የተሰጠውን ትርጉም ይይዛል፡፡

18) **“ታክስ”** ማለት ወደ አገር በሚገቡ እቃዎች ላይ የሚሰበሰብ የተጨማሪ እሴት ታክስ ነው፡፡

19) **“የጉምሩክ አዋጅ”** ማለት የጉምሩክ አዋጅ (እንደተሻሻለው) ቁጥር 859/2006 ነው፡፡

20) **“ሚኒስቴር” ወይም “ሚኒስትር”** ማለት እንደ ቅደም ተከተሉ የገንዘብ ሚኒስቴር ወይም ሚኒስትር ነው፡፡

21) በዚህ ደንብ ውስጥ ማንኛውም በወንድ ጾታ የተቀመጠው አገላለጽ ሁሉ የሴትንም ጾታ ይጨምራል፡፡

3. የተፈፃሚነት ወሰን

1) የዚህ ደንብ ድንጋጌዎች ታክስ ማበረታቻ በሚያስገኙ የኢንቨስትመንት መስኮች የሚሰማራ ኢንቨስትመንትን ለማበረታታት በሚሰጡ ማበረታቻዎች ላይ ተፈፃሚ ይሆናሉ፡፡

2) በዚህ ደንብ ክፍል አራት የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የዚህ ደንብ ሌሎች ድንጋጌዎች በማዕድን፤ በነዳጅ፣ በተፈጥሮ ጋዝ እና በጂኦተርማል ኢንቨስትመንት ላይም ተፈፃሚነት ይኖራቸዋል፡፡

4. አላማዎች

በዚህ ደንብ መሰረት የሚፈቀዱ የታክስ ማበረታቻዎች፤

CamScanner

ሀ/ አምራች ኢንቨስትመንትን፤

ለ/ የወጪ ንግድን፤

ሐ/ የቴክኖሎጂ ዝውውርን፤

መ/ የስራ ፈጠራን፤

ሠ/ የከባቢ አየር ደህንነት ጥበቃን፤

ረ/ የሀገሪቱ የ የተፈጥሮ ሀብት በውጤታማ እና በብቃት መልማትን፤እና

ሰ/ የክልሎችን እድገት የማበረታታት አላማ ይኖራቸዋል።

5. መርሆዎች

ኢንቨስትመንትን ለማበረታታት የሚሰጥ የታክስ ማበረታቻ የሚከተሉትን መርሆዎች በአንድነት የተከተለ መሆን አለበት፦

1) በህግ ላይ የተመሰረተ፤ ግልጽ፤ በጊዜ የተገደበ፤
2) የመንግስትን የፋይናንስ አቅም መሰረት ያደረገ፤
3) በጽሁፍ ይፋ በተደረገ መስፈርት መሰረት አድልዎ በሌለበት ሁኔታ የሚሰጥ፤
4) የታቀደውን ውጤት ያስገኘ መሆኑ ክትትል የሚደረግበት፤ እና
5) ህግ ተጥሶ በሚገኝበት ጊዜ የሚሰረዝና ተጠያቂነትን የሚያስከትል።

ክፍል ሁለት

የተፈቀዱ ማበረታቻዎች እና ቅድመ-ሁኔታዎች

6. የተፈቀዱ ማበረታቻዎች

በዚህ ደንብ በተደነገገው መሰረት የሚከተሉት የማበረታቻ አይነቶች እንደሁኔታው ለፈቀዱ ይችላሉ፦

1) የኢንቨስትመንት የካፒታል ወጪ ተቀናሽ (አላዋንስ)፣
2) ከመደበኛው የማስከፈያ መጣኔ ዝቅ ያለ የገቢ ግብር፤
3) ከአማራጭ አነስተኛ ግብር ነፃ የመሆን፣
4) በዲቪደንድ ላይ ከሚከፈል ነፃ የመሆን፤
5) ከካፒታል ዋጋ ዕድገት ግብር ላይ ነፃ የመሆን፤
6) ሊከፈል ከሚገባ የገቢ ግብር ላይ ተቀናሽ የማግኘት፤ እና
7) የጉምሩክ ቀረጥ እና ታክስ ማበረታቻ።

CamScanner

7. ማበረታቻ የሚሰጥባቸው ሁኔታዎች

በዚህ ደንብ የተመለከቱት ማበረታቻዎች የሚሰጡት በሚከተሉት ሁኔታዎች ይሆናል፦

1) ተጨማሪ አቅም ወይም እሴት ለሚፈጥሩ አዲስ ኢንቨስትመንቶች፤

2) አመልካቹ በታክስ ከፋይነት የተመዘገበ፤ ተፈላጊ ሁኔታዎችን የሚያሟላ እና ለያንዳንዳንዱ ማበረታቻ ለሚሰጠው ፕሮጀክት ወይም የስራ ዘርፍ የተለየ የሂሳብ መዝገብ የሚያቀርብ ሲሆን፤

3) ማበረታቻዎቹ ለተቋቋሙለት ገቢ እና ለተፈቀዱት ወጪዎች ብቻ የሚውሉ መሆኑን ለማረጋገጥ በሚያስችል አኳኋን የታጠረ ስርአት በመዘርጋት፤

4) በዚህ ደንብ በተፈቀደው መሰረት ካልሆነ በስተቀር ለተወሰነ ጊዜ እና ለሌላ ወገን ማስተላለፍ በማያስችል አኳኋን፤ እና

5) በዚህ ደንብ እና ደንቡን ተከትሎ በሚወጡ መመሪያዎች በስተቀር ተደራራቢ ማበረታቻ እንዲኖር በማያስችል ሁኔታ።

ክፍል ሶስት

የገቢ ግብር ማበረታቻ

8. ለልዩ የኢኮኖሚ ዞን አልሚ እና ንዑስ አልሚ የሚሰጥ የገቢ ግብር ማበረታቻ

1) የልዩ ኢኮኖሚ ዞን አልሚ እና ንዑስ አልሚ፤

ሀ) በአዲስ አበባ እና በኦሮሚያ ሸገር ከተማ አስተዳደር የሚቋቋሙ ግብር ከሚከፈልበት አመታዊ ገቢያቸው ላይ ስራ ከጀመሩበት ቀን ጀምሮ ለሚቆጠሩ አስር አመታት (10) አመታት የ5% (አምስት በመቶ) የቅናሽ የገቢ ግብር መጣኔ፤ ፤ ከዚያ በኋላ ባሉት አመታት በገቢ ግብር አዋጅ በተደነገገው መሰረት የንግድ ትርፍ ግብር ይከፍላሉ።

ለ) በፊደል ተራ "ሀ" ከተገለጹት ቦታዎች ውጪ የሚቋቋሙ ግብር ከሚከፈልበት አመታዊ ገቢያቸው ላይ ስራ ከጀመሩበት ቀን ጀምሮ ለሚቆጠሩ አስራ አምስት አመታት (15) አመታት የ5% (አምስት በመቶ) የቅናሽ የገቢ ግብር መጣኔ፤ ከዚያ በኋላ ባሉት አመታት በገቢ ግብር አዋጅ በተደነገገው መሰረት የንግድ ትርፍ ግብር ይከፍላሉ።

ሐ) ለባለአክሲዮኖች በሚከፍሉት የትርፍ ድርሻ ላይ ከሚከፈል ታክስ ለአምስት (5) አመታት ነጻ ይሆናሉ።

CamScanner

መ) ከአማራጭ አነስተኛ ግብር ለአስር (10) አመታት ነጻ ይሆናሉ።

2) በልዩ የኢኮኖሚ ዞን አዋጅ መሰረት የኢንቨስትመንት ቦርድ በልዩ ሁኔታ ካልወሰነ በስተቀር የልዩ ኢኮኖሚ ዞን አልሚ እና ንዑስ አልሚ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተዘረዘሩትን ማበረታቻዎች ተጠቃሚ ሊሆኑ የሚችሉት ቢያንስ 75,000,000 (ሰባ አምስት ሚሊዮን) የአሜሪካን ዶላር ስራ ላይ ማዋላቸው ሲረጋጋጥ ይሆናል።

9. ለልዩ የኢኮኖሚ ዞን ድርጅት የሚሰጥ የገቢ ግብር ማበረታቻ

1) በአዲስ አበባ እና በኦሮሚያ ሸገር ከተማ የሚቋቋም የልዩ ኢኮኖሚ ዞን ድርጅት በሰንጠረዥ 1 በተጠቀሰው መሰረት የ15% (አስራ አምስት በመቶ) የቅናሽ የገቢ ግብር መጣኔ ፤ ከዚያ በኋላ ባሉት አመታት በገቢ ግብር አዋጅ በተደነገገው መሰረት የንግድ ትርፍ ግብር ይከፍላል።

2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ከተጠቀሱት ቦታዎች ውጪ የሚቋቋም የልዩ ኢኮኖሚ ዞን ድርጅት ግብር ከሚከፈልበት አመታዊ ገቢው ላይ ስራ ከጀመረበት ቀን ጀምሮ ለሚቆጠሩ አስር (10) አመታት 10% (አስር በመቶ)፤ ከዚያ በኋላ ባሉት አመታት በገቢ ግብር አዋጅ በተደነገገው መሰረት የንግድ ትርፍ ግብር ይከፍላል።

3) የልዩ ኢኮኖሚ ዞን ድርጅት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተመላከተውን ማበረታቻ ተጠቃሚ ሊሆን የሚችለው በዚህ ደንብ አንቀጽ 13 በተዘረዘሩት መስኮች የተሰማራ ሲሆን ነው።

10. ለስታርታፕ የሚሰጥ የገቢ ግብር ማበረታቻ

አግባብነት ባለው ሕግ ስያሜ የተሰጠው ስታርታፕ፤

ሀ) ስራ ከጀመረበት ጊዜ ጀምሮ ለሚቆጠር የ10 አመት አስር አመት) ጊዜ ግብር በሚከፈልበት ገቢው ላይ 5% (አምስት በመቶ) የቅናሽ ገቢ ግብር ማስከፈያ መጣኔ፤ ከዚያ በኋላ በገቢ ግብር አዋጅ በተደነገገው መሰረት የንግድ ትርፍ ግብር ይከፍላል።

ለ) ለባለአክሲዮኖች በከሚከፍለው የትርፍ ድርሻ ላይ ከሚከፈል ታክስ ለአምስት (5) አመታት ነጻ ይሆናል።

11. ለስታርታፕ ምህዳር ገንቢ የሚሰጥ ማበረታቻ

አግባብነት ባለው ሕግ እውቅና የተሰጠው የስታርታፕ ምህዳር ገንቢ፤

ሀ/ በስታርታፕ ውስጥ ያለውን የባለቤትነት ድርሻ በመሸጥ የሚያገኘው የካፒታል ዋጋ እድገት ጥቅም ግብር አይከፈልበትም።

ለ) ከስታርታፕ በሚቀበለው የትርፍ ድርሻ ላይ ከሚከፈል ታክስ ለአምስት (5) አመታት ነጻ ይሆናል።

CamScanner

ሐ) በስታርታፕ ውስጥ ባለሀብት በመሆኑ ኪሳራ የደረሰበት መሆኑን ማሳየት እስከቻለ ድረስ ከአማራጭ አነስተኛ ግብር ለሦስት (3) አመታት ነጻ ይሆናል።

12. ለአካባቢ አየር ደህንነት ጥበቃ የሚሰጥ ማበረታቻ

1) በካርቦን ልውውጥ ገበያ ወይም በበካይ ጋዝ አመንጪ የገበያ ስርአት ውስጥ ተሳታፊ የሆኑ እና በአካባቢ ደህንነት ጥበቃ ባለስልጣን እውቅና የተሰጣቸው ኩባንያዎች ስራ ከጀመሩበት ጊዜ ጀምሮ ለ10 (አስር) አመታት ግብር በሚከፈልበት ገቢያቸው ላይ 15% (አስራ አምስት በመቶ) የንግድ ትርፍ ግብር ይከፍላሉ።

2) በምርት ወይም የአሰራር ሂደቱ ቢያንስ ሃምሳ በመቶ (50%) ታዳሽ ኃይል የሚጠቀም ማንኛውም ባለሀብት፣ ስራ ከጀመረበት ጊዜ አንስቶ ላሉት ተከታታይ አምስት (5) ዓመታት ብቻ ግብር በሚከፈልበት ገቢያቸው ላይ 15% (አስራ አምስት በመቶ) የንግድ ትርፍ ግብር ይከፍላሉ።

3) ማበረታቻው ብቁ ለመሆን ባለሀብቱ በውሃና ኢነርጂ ሚኒስቴር የሚሰጥ የአረንጓዴ ኃይል አጠቃቀም የምስክር ወረቀት ማግኘት ይኖርበታል። ይህንንም ለማረጋገጥ የተቀመጠውን የታዳሽ ኃይል አጠቃቀም መጠን ማሟላቱን የሚያረጋግጡ ዓመታዊ የኃይል ኦዲት ሪፖርቶችን ማቅረብ ይኖርበታል።

13. ከልዩ የኢኮኖሚ ዞን ውጪ የተሰማሩ ኢንቨስተሮች የገቢ ግብር ማበረታቻ

1) ከልዩ የኢኮኖሚ ዞን ውጪ በቆዳ እና ጨርቃ ጨርቅ አምራች ኢንዱስትሪ፤ በኬሚካልና ኬሚካል ውጤቶች ኢንዱስትሪ፤ በመሰረታዊ መድሃኒት ምርትና የመድሃኒት ኢንዱስትሪ፤ የመሰረታዊ ብረታ ብረት (ማሽነሪ ማምረትን ጨምሮ) ኢንዱስትሪ፤ ብረት ያልሆኑ የማዕድን ውጤቶች ኢንዱስትሪ፤ የኮምፒዩተር፣ የኤሌክትሮኒክስ እና የዕይታ ዕቃዎች ኢንዱስትሪ፤ የኤሌትሪክ ዕቃዎች ኢንዱስትሪ፤ የመጓጓዣ ተሽከርካሪዎች እና ሌሎች የትራንስፖርት መሳሪያዎችን ማምረትና ወይም መገጣጠም፤ የእንጨት ውጤቶች ኢንዱስትሪ፣ የወረቀት ኢንዱስትሪ፤ አግሮ ፕሮሰሲንግ፤ ፓኬጂንግ ብሎም ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ልማት መስክ፤ የኤሌትሪክ ሃይል ማመንጨት፤ ማስተላለፍና ማከፋፈል፤ ላይ የተሰማሩ ባለሀብቶች በዚህ ደንብ ሰንጠረዥ 1 የተመለከተውን የቅናሽ የገቢ ግብር መጣኔ ማበረታቻ ያገኛሉ።

2) ሚኒስቴሩ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ከተመላከቱ ዘርፎች ውስጥ የሚካተቱትን እና ለገቢ ግብር ማበረታቻ ብቁ የሚሆኑትን ንዑስ ዘርፎች በመመሪያ ይወስናል።

CamScanner

14. የኢንቨስትመንት ካፒታል አላዋንስ

1) ከዚህ ደንብ ጋር አባሪ በሆነው ሰንጠረዥ 2 ለተዘረዘሩ የኢንቨስትመንት መስኮች ለካፒታል እቃዎች ለወጣ ተቀባይነት ያለው ወጪ በሰንጠረዡ መሰረት የኢንቨስትመንት ካፒታል አላዋንስ ይፈቀዳል።

2) የኢንቨስትመንት ካፒታል አላዋንስ ተጠቃሚ ለመሆን የሚችሉት ቢያንስ አንድ ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር (1,000,000,000 የአሜሪካን ዶላር) በኢንቨስትመንት ስራ ላይ ያዋሉ ኢንቨስተሮች ብቻ ናቸው።

3) የኢንቨስትመንት ካፒታል አላዋንስ የሚፈቀደው በሚከተለው ሁኔታ ይሆናል፦

ሀ) የካፒታል እቃው በግብር ከፋዩ ባለቤትነት ስም ያለ ወይም በካፒታል ዕቃዎች ኪራይ የተያዘ ከሆነ፤

ለ) የካፒታል ዕቃው ሙሉ በሙሉ እና በብቸኝነት ግብር የሚከፈልበትን ገቢ ለማግኘት የዋለ ከሆነ፤ ወይም ሙሉ በሙሉ ወይም በብቸኝነት ግብር የሚከፈልበትን ገቢ ለማግኘት ያልዋለ ከሆነ፤ ታክስ ለሚከፈልበት ገቢ የዋለውን መጠን በትክክል ለይቶ በማስላት በዚያው መጠን ብቻ፤

ሐ) ለመደበኛ ወጪ ሳይሆን በትክክል ለካፒታል ወጪ በዋለው መጠን ብቻ፤

መ) የካፒታል እቃው ከተፈራበት ጊዜ ጀምሮ ሳይሆን ወይም ያለአገልግሎት በተቀመጠበት ጊዜ ጭምር ሳይሆን፤ገቢ በሚያመነጭበት ጊዜ ብቻ፤ እና

ሠ) ግብር ከፋዩ ትክክለኛ የሂሳብ መዝገብ የሚይዝ ከሆነ።

15. ምርቱን ወይም አገልግሎቱን ወደ ውጭ ለሚልክ ባለሀብት የሚሰጥ የገቢ ግብር ማበረታቻ

1) ከልዩ የኢኮኖሚ ዞን ውጪ ያለ ኢንቨስትመንት ሆኖ ምርቱን ወይም አገልግሎቱን ወደ ውጭ የሚልክ ባለሀብት በዚያው የግብር አመት ግብር በሚከፈልበት ገቢው ላይ 10% (አስር በመቶ) የንግድ ትርፍ ግብር ይከፍላል።

2) በልዩ የኢኮኖሚ ዞን ውስጥ ኢንቨስት ያደረገ ባለሀብት ካቋቋመው የማምረቻ ፋብሪካ ምርቱን ወደ ውጭ ሲልክ በዚያው የግብር አመት ግብር በሚከፈልበት ገቢው ላይ 5% (አምስት በመቶ) የንግድ ትርፍ ግብር ይከፍላል።

CamScanner

16. ለሳይንሳዊ ምርምር የሚሰጥ ማበረታቻ

1) ማናቸውም ባለሀብት በንግድ ስራው ገቢ ውስጥ የተካተተውን ገቢ ለማግኘት በአንድ የግብር አመት ውስጥ ከንግድ ስራው እንቅስቃሴ ጋር በተያያዘ ለሳይንሳዊ ምርምር የሚያወጣው ወጪ ተቀናሽ ይደረጋል።

2) ለዚህ አንቀጽ አፈጻጸም፦

   ሀ) **"ሳይንሳዊ ምርምር"** ማለት የሰውን ልጅ እውቀት ለማሻሻል በተፈጥሮ ወይም ተግባራዊ ሳይንስ ረገድ የሚከናወን ማናቸውም እንቅስቃሴ ነው።

   ለ) **"የሳይንሳዊ ምርምር ወጪ"** ማለት የንግድ ስራ የሚያካሂድን ሰው በሚመለከት የንግድ ስራውን ለማሳደግ ለሚጠቀምበት የሳይንሳዊ ምርምር ተቋም የንግድ ስራውን ለማሳደግ ለሚደረግ ሳይንሳዊ ምርምር የሚያደረገውን መዋጮ የሚጨምር ሲሆን፤ የሚከተሉትን አያካትትም፦

      i) የእርጅና ቅናሽ ለሚደረግለት ንብረት ወይም ግዙፋዊ ሃልዎት ለሌለው ንብረት የሚወጣ ወጪ፤

      ii) ለመሬት ወይም ለህንጻ የሚወጣ ወጪ፤

      iii) የተፈጥሮ ሃብት ስለመኖሩ፣ ያለበትን ቦታ፤ ብዛት ወይም ጥራቱን ለማወቅ የሚወጣ ወጪ፤ እና

   ሐ) **"የሳይንሳዊ ምርምር ተቋም"** ማለት የሳይንሳዊ ምርምር ለማድረግ የተቋቋመ ማህበር፤ ኢንስቲትዩት ወይም ከፍተኛ የትምህርት ተቋም ነው።

17. በገቢ ግብር ማበረታቻ ዘመን ገቢን ስለማሳወቅ

1) ማንኛውም ባለሀብት በዚህ ደንብ የተመለከቱት የገቢ ግብር ማበረታቻዎች ተጠቃሚ የሚሆነው በገቢ ግብር አዋጅ በተደነገገው መሠረት የሂሳብ መዝገቡን አግባብ ላለው የታክስ ባለስልጣን ሲያቀርብ ይሆናል።

2) ማንኛውም ባለሀብት የገቢ ግብር ማበረታቻ የሚያስገኙ ሁለት እና ከዚያ በላይ በሆኑ የኢንቨስትመንት መስኮች ላይ የተሰማራ እንደሆነ ለታክስ ማበረታቻ ዓላማ የእያንዳንዱን ኢንቨስትመንት ገቢ ለየብቻ ማሳወቅ አለበት።

3) የገቢ ግብር ማበረታቻ ተጠቃሚ የሆነ ባለሀብት በገቢ ግብር አዋጅ በተደነገገው መሠረት የሂሳብ መዝገቡን ያላቀረበ እንደሆነ ግዴታውን ላልተወጣበት የግብር ዘመን የግብር ማበረታቻ ተጠቃሚ መሆኑ ቀሪ ይሆናል።

4) ባለሀብቱ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 1 የተደነገገውን ግዴታው ያልተወጣው ሚኒስቴሩ በሚያወጣው መመሪያ በተመለከተ ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት ከሆነ የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 3 ተፈፃሚነት አይኖረውም።

CamScanner

18. የገቢ ግብር ማበረታቻ ስለሚጀምርበት ጊዜ

1) የገቢ ግብር ማበረታቻ መቆጠር የሚጀምረው ባለሀብቱ ስራ ከጀመረበት ወይም የንግድ ሥራ ፈቃድ ከወሰደበት ቀን አንስቶ ይሆናል፡፡

2) ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) አፈፃፀም አግባብ ያለው መስሪያ ቤት ባለሀብቱ ስራ የጀመረበትን፤ የንግድ ሥራ ፈቃድ የወሰደበትን ቀን ለታክሱ ባለስልጣን ያሳውቃል፡፡

3) ማንኛውም ባለሀብት ማምረት ወይም አገልግሎት መስጠት ጀምሮ ግብር የከፈለ እንደሆነና ከዚህ በኋላ የገቢ ግብር ማበረታቻ ተጠቃሚ መሆኑን የሚገልፅ ደብዳቤ ያመጣ እንደሆነ የከፈለውን ግብር ተመላሽ መጠየቅ አይችልም፡፡

19. ተጠቃሚነት ላይ ስለሚጣል ገደብ

የኢንቨስትመንት ማበረታቻ የሚያስገኝ ኢንቨስትመንት ባለቤት የሆነ ሰው የተሠማራበትን ኢንቨስትመንት ዘግቶ ተመልሶ የኢንቨስትመንት ማበረታቻ በሚያሰጥ ኢንቨስትመንት ላይ ከተሰማራ ቢያንስ በዘጋው ኢንቨስትመንት የተጠቀመበትን የኢንቨስትመንት ማበረታቻ ለሚያክል ጊዜ የገቢ ግብር ማበረታቻ ተጠቃሚ አይሆንም፡፡ ዝርዝሩ ሚኒስቴሩ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል፡፡

ክፍል አራት

የጉምሩክ ቀረጥ እና ታክስ ማበረታቻ

20. ለልዩ ኢኮኖሚ ዞን አልሚ፣ አስተዳዳሪ እና ድርጅቶች ስለሚሰጥ የጉምሩክ ቀረጥ እና ታክስ ማበረታቻ

1) የኢንቨስትመንት ፈቃድ የተሰጣቸው አልሚዎች፣ አስተዳዳሪዎች እና ድርጅቶች ወደ አገር የሚያስገቧቸው የካፒታል እና የግንባታ ዕቃዎች፣ ጥሬ ዕቃዎች እንዲሁም መለዋወጫዎች የጉምሩክ ቀረጥ እና ታክስ ማበረታቻ ተጠቃሚ ሆነው ወደ አገር ሊገቡ ይችላሉ፡፡

2) የኢንቨስትመንት ፈቃድ የተሰጣቸው አልሚዎች፣ አስተዳዳሪዎች እና ድርጅቶች በቀጥታ፣ በተቋራጭ ወኪሉ ወይም በተመዘገበ የሎጂስቲክስ ኦፕሬተር አማካኝነት ለራሳቸው ኢንቨስትመንት አገልግሎት የተገዙ የግንባታ ዕቃዎችን እና የካፒታል ዕቃዎችን የጉምሩክ ቀረጥ እና ታክስ ማበረታቻ ተጠቃሚ በመሆን ወደ ልዩ ኢኮኖሚ ዞን ማስገባት ይችላሉ፡፡

3) በዚህ አንቀጽ 1 እና 2 መሰረት የልዩ ኢኮኖሚ ዞን አልሚ፣ አስተዳዳሪ እና ድርጅቶች ወደ አገር የሚያስገቧቸው ዕቃዎች የጊዜ እና የመጠን ገደብ ሳይደረገባቸው የንግድ ፈቃድ ከወጣ በኋላ ዕቃዎች ወደ አገር ሊገቡ ይችላሉ፡፡

CamScanner

21. የካፒታልና የግንባታ ዕቃዎች የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ማበረታቻ ስለመሆን

1) ከዚህ ደንብ ጋር በተያያዘው ሠንጠረዥ 3 (ሦስት) ከተዘረዘሩት የሥራ መስኮች በአንዱ የተሠማራ ባለሀብት የካፒታልና የግንባታ ዕቃዎችን የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ማበረታቻ ተጠቃሚ በመሆን ወደ አገር ማስገባት ይችላል፡፡

2) ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) አፈፃፀም ባለሀብቱ የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ማበረታቻ ተጠቃሚ ሆኖ ወደ አገር እንዲገቡ የሚፈልጋቸውን የካፒታልና የግንባታ ዕቃዎች ዝርዝር ወይም እንደአግባብነቱ ዝርዝሮቹን የሚያስረዳ ሰነድ እና ግንባታው የሚጠይቀውን ግብዓቶች አይነትና መጠን የሚያሳይ የፀደቀ የተፈላጊ ዕቃ ብዛት ሰነድ በሕግ ስልጣን ለተሰጠው አካል በማቅረብ ማስፈቀድ ይኖርበታል፡፡

3) የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ማበረታቻ ተጠቃሚ የሆነ ባለሀብት ከአገር ውስጥ የማምረቻ ኢንዱስትሪዎች ወይም ከአስመጪ የካፒታል ወይም የግንባታ ዕቃዎችን ሲገዛ ዕቃዎቹን ለማምረት በግብዓትነት በዋሉት ጥሬዕቃዎች ወይም ግብዓቶች ላይ የተከፈለው የጉምሩክ ቀረጥ ተመላሽ ይደረጋል፡፡

4) በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 1 መሰረት የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ማበረታቻ ተጠቃሚ ሆነው እንዲገቡ የሚፈቀዱ የካፒታል እና የግንባታ ዕቃዎች ዝርዝር ሚኒስቴሩ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል፡፡

5) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሰረት ባለሀብቱ የካፒታል እና የግንባታ ዕቃዎችን የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ማበረታቻ ተጠቃሚን ሆኖ ወደ አገር ማስገባት የሚችለው የንግድ ፈቃድ እስከሚያወጣ ባለው ጊዜ ውስጥ ብቻ ይሆናል፡፡

6) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 5 የተደንገገው ቢኖርም ኢንቨስትመንቱ በየምዕራፉ የሚከናወን ሲሆን እና ለእያንዳንዱ ምዕራፍ የተለያዩ የካፒታል እና የግንባታ ዕቃዎችን በተለያዩ ጊዜያት ወደ አገር ማስገባት አስፈላጊ ሲሆን፣ ይህም በባለሀብቱ የቢዝነስ ዕቅድ እና በአንቀጽ 25 መሰረት በተገባው የአፈፃፀም ስምምነት ላይ የተመላከተ ከሆነ፣ ባለሀብቱ የንግድ ፈቃድ ካወጣ በኋላ ለሚቀጥሉት ምዕራፎች የካፒታል እና የግንባታ ዕቃዎችን የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ማበረታቻ ተጠቃሚ በመሆን ሊያስገባ ይችላል፡፡

7) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 6 መሰረት ተጠቃሚ ለመሆን ከባለሀብቱ ጥያቄ ሲቀርብ ለቀደመው ምዕራፍ ለባለሀብቱ የተፈቀደው የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ማበረታቻ መብት ለታለመለት ዓላማ የዋለ ስለመሆኑ እና ባለሀብቱ የገባውን የአፈፃፀም ውል ያከበረ ስለመሆኑ በቅድሚያ ሊጣራ ይገባዋል፡፡

22. ተሸከርካሪዎች የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ማበረታቻ ተጠቃሚ መሆን

1) ለኢንቨስትመንት ዓላማ የሚውሉ ተሸከርካሪዎች የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ማበረታቻ ተጠቃሚ ሆነው ወደ አገር የሚገቡበት ሁኔታ የኢንቨስትመንት

CamScanner

ፕሮጀክቶችን ዓይነትና ባህሪ መሠረት በማድረግ ሚኒስቴሩ በሚያወጣው መመሪያ የሚወሰን ይሆናል።

2) ሚኒስቴሩ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሰረት የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ማበረታቻ ተጠቃሚ ሆነው እንዲገቡ ሊፈቅድ የሚችለው ከፒክ አፕ እና ስቴሽን ዋገን ውጪ ያሉ ተሽከርካሪዎችን ነው።

3) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 የተመለከተው ቢኖርም የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ቦርድ ከመሃል አገር ርቀት ባላቸው አካባቢዎች በማዕድን፣ በነዳጅ፣ በተፈጥሮ ጋዝ፣ በግብርና እና በቱሪዝም ሥራ ላይ የተሰማሩ ድርጅቶች የሚጠቀሙባቸውን ፒክ አፕ እና ስቴሽን ዋገን ተሽከርካሪዎች የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ማበረታቻ ተጠቃሚ ሆነው ወደ አገር እንዲያስገቡ ሊፈቅድ ይችላል።

23. የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ማበረታቻ ተጠቃሚ ሆኖ የገባ ዕቃን ስለማስተላለፍ

1) የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ማበረታቻ ተጠቃሚ ሆኖ የገባ የካፒታል ዕቃ ወይም የግንባታ ዕቃ አስቀድሞ ተገቢውን የጉምሩክ ቀረጥ በመክፈል የጉምሩክ ቀረጥ ነፃ መብት ለሌለው ሰው ሊተላለፍ ይችላል።

2) ባለሀብቱ የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ማበረታቻ ተጠቃሚ ሆኖ ያስገባውን የካፒታል ዕቃ ወይም የግንባታ ዕቃ መልሶ ከአገር እንዲወጣ ማድረግ ይችላል።

3) በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 1 መሰረት የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ማበረታቻ ተጠቃሚ ሆኖ ወደ አገር ውስጥ የገባ ዕቃ የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ማበረታቻ መብት ላለው ሰው ሊተላለፍ ይችላል።

4) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 መሰረት የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ማበረታቻ ተጠቃሚ ሆኖ ወደ አገር ውስጥ የገባ ዕቃ የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ማበረታቻ መብት ላለው ሰው ሊተላለፍ የሚችለው ሚኒስቴሩ በሚያወጣው መመሪያ የተወሰኑት ለማስተላለፍ የሚያስገድዱ ሁኔታዎች ሲሟሉ ይሆናል።

5) የዚህን አንቀጽ ድንጋጌዎች የተላለፈ ማንኛውም ባለሀብት አግባብ ባለው የጉምሩክ አዋጅ ድንጋጌ መሠረት ተጠያቂ ይሆናል።

ክፍል አምስት

የማዕድን፣ ነዳጅ እና የጂኦተርማል ሥራዎች

24. ለማዕድን ኢንቨስትመንት የሚሰጥ ማበረታቻ

1) የማዕድን ስራዎች

ሀ) ማንኛውም የምርመራ ባለፈቃድ ወይም የእርሱ ተቋራጭ ለስራው የሚያስፈልጉና በፀደቀው የስራ ፕሮግራም መሰረት

CamScanner

ከውጭ አገር ወደ ኢትዮጵያ የሚያስገባቸው መሳሪያዎች፣ የግንባታ ዕቃዎች፣ ማሽነሪዎች እና አላቂ ዕቃዎች የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ማበረታቻ ተጠቃሚ ይሆናሉ፡፡

ለ) ማንኛውም የአነስተኛ ወይም የከፍተኛ ደረጃ የማዕድን ማምረት ባለፈቃድ ወይም የእርሱ ተቋራጭ ለስራው የሚያስፈልጉና በፀደቀው የስራ ፕሮግራም መሰረት ከውጭ አገር ወደ ኢትዮጵያ የሚያስገባቸው የማምረት ስራውን ለመጀመር የሚያስችሉ መሳሪያዎች፣ የግንባታ ዕቃዎች፣ ማሽነሪዎች እና አላቂ ዕቃዎች የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ማበረታቻ ተጠቃሚ ይሆናሉ፡፡

ሐ) የአነስተኛ ወይም የከፍተኛ ደረጃ የማዕድን ማምረት ባለፈቃድ የምርት ስራውን በላቀ ደረጃ ለማስፋፋት ሲፈልግና የማስፋፊያው ዕቅድ በፈቃድ ሰጪው ባለስልጣን ሲፀድቅ ለማስፋፊያ ስራው የሚያስፈልጉ መሳሪያዎችን፤ የግንባታ ዕቃዎችን፣ ማሽነሪዎችን እና አላቂ ዕቃዎችን የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ማበረታቻ ተጠቃሚ ሆኖ ማስገባት ይችላል፡፡

መ) የባህላዊ ማዕድን ማምረት ባለፈቃድ ወይም አሸዋ ወይም ገረጋንቲ ለማምረት የሚያስችል ፈቃድ ያለው ማንኛውም የኮንስትራክሽን ማዕድን ማምረት ባለፈቃድ በዚህ ንዑስ አንቀፅ ተራ ፊደል ሀ ፣ ለ እና ሐ የተመለከቱት የጉምሩክ ቀረጥ ነፃ መብት ተጠቃሚ አይሆንም፡፡

ረ) የማዕድን ምርመራ ስራ ባለፈቃድ ለማዕድን ስራው አግባብነት ያላቸውን መረጃዎች ለመሰብሰብ የሚያስፈልግ አውሮፕላን፤ ሄሊኮፕተር፤ ድሮን እና/ወይም ሌሎች ለስራው አግባብነት ያላቸውን የመመርመሪያ መሳሪያዎች ከተቆጣጣሪው ባለስልጣን ድጋፍ ሲያገኝ የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ማበረታቻ ተጠቃሚ ሆኖ ወደ አገር ውስጥ ማስገባት ይችላል፡፡

ሠ) ማንኛውም ባለፈቃድ የተፈቀዱለትን መሳሪያዎች እና ማሽነሪዎች በማዕድን ማምረት ቅድመ ዝግጅት ጊዜ ማስገባት ካልቻለ ማዕድን ማምረት ከጀመረ በኋላ እስከ አምስት ዓመት ባለው ጊዜ ውስጥ የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ማበረታቻ ተጠቃሚ ሆኖ ወደ አገር ለማስገባት ይችላል፡፡

2) በማዕድን ዋጋ ላይ ተጨማሪ እሴት ማከል፡ -

ሀ) ማንኛውም የመቅረፅ ዕደ ጥበብ ባለፈቃድ ወይም የማጣራት ባለፈቃድ ለውጭ ገበያ የሚቀርብ የማዕድን ምርት የሚያመርት ከሆነ በፀደቀው የስራ ፕሮግራም መሰረት ለስራው ከውጭ ሀገር ወደ ኢትዮጵያ የሚያስገባቸው መሳሪያዎች እና ማሽነሪዎች የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ማበረታቻ ተጠቃሚ ይሆናሉ፡፡

ለ) በዚህ ንዑስ አንቀፅ ፊደል ተራ (ሀ) የተደነገገው ቢኖርም የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ማበረታቻ ተጠቃሚ ሆኖ ማስገባት

CamScanner

መብት ፀንቶ የሚቆየው ፈቃዱ ከተሰጠበት ቀን አንስቶ ለ 3 (ሦስት) ዓመት ብቻ ይሆናል።

3) የነዳጅ፣ የተፈጥሮ ጋዝ እና የጂኦተርማል ስራዎች፤

ሀ) ማንኛውም የምርመራ ባለፈቃድ ወይም የእርሱ ተቋራጭ ለስራው የሚያስፈልጉና በፀደቀው የስራ ፕሮግራም መሰረት ከውጭ አገር ወደ ኢትዮጵያ የሚያስገባቸው መሳሪያዎች፣ የግንባታ ዕቃዎች፣ ማሽነሪዎች እና አላቂ ዕቃዎች የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ማበረታቻ ተጠቃሚ ይሆናሉ።

ለ) ማንኛውም የነዳጅ ወይም የጂኦተርማል ማምረት ባለፈቃድ ወይም የእርሱ ተቋራጭ ወደ ኢትዮጵያ የሚያስገባቸው የቁፋሮ፣ የጂኦሎጂካል፣ የጂኦፊዚካል፣ የማምረቻ፣ የማዘጋጃ፣ የማጣሪያ፣ ማጓጓዣ እና ሌሎች ለነዳጅ ስራዎች አስፈላጊ የሆኑ መሳሪያችና ዕቃዎች፣ የአየር፣ የባሕር መጓጓዣዎችን እና ሌሎች የመጓጓዣ መሳሪያዎችንና መለዋወጫቸውን ጨምሮ ለስራው ማስፈሚያ የሚያስፈልገውን ነዳጅ፣ ኬሚካሎች፣ ዘይት፣ ቅባትና መለዋወጫዎች፣ ፊልሞች፣ ሳይዝሚክ ቴፖች፣ ተንቀሳቃሽ ቤቶች፣ ተንቀሳቃሽ ቢሮዎችና ተገጣጣሚ ስትራክቸሮች የተፈታቱ ክፍሎች እና ለነዳጅ ስራ አስፈላጊ የሆኑ ሌሎች ቁሳቁሶች የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ማበረታቻ ተጠቃሚ ይሆናሉ፡ :

ሐ) የውጭ ሀገር የሆኑ የነዳጅ ባለፈቃዱ ወይም የተቋራጩ ተቀጣሪ ሰራተኞች ወደ ኢትዮጵያ የሚያስገቧቸው የቤት ዕቃዎችና የግል መገልገያዎች አግባብነት ባላቸው ሕጎች መሰረት የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ማበረታቻ ተጠቃሚ ይሆናሉ።

4) በዚህ አንቀጽ የተመለከተው ቢኖርም የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ቦርድ ስትራቴጂክ ለሆኑ እና ለእሴት ጭማሪ አጋዥ ለሆኑ የማዕድን ወይም የነዳጅ ምርቶችና ሥራዎች ተጨማሪ ማበረታቻ ሊፈቅድ ይችላል።

5) የባዮፊዩል ስራዎች

ሀ) የባዮፊዩል ልማት ባለፈቃድ እንደፈቃዱ ዓይነት በፀደቀው የስራ ፕሮግራም መሰረት ለስራው የሚያስፈልጉ ከውጭ ሀገር ወደ ኢትዮጵያ የሚያስገባቸው መሳሪያዎችና ማሽነሪዎች የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ማበረታቻ ተጠቃሚ ይሆናሉ፣

ለ) በዚህ ንዑስ አንቀፅ ፊደል ተራ (ሀ) የተደነገገው ቢኖርም የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ማበረታቻ የማስገባት መብት ፀንቶ የሚቆየው ፈቃዱ ከተሰጠበት ቀን አንስቶ ለ5 ዓመት ብቻ ይሆናል።

6) በዚህ አንቀፅ መሰረት የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ማበረታቻ ተጠቃሚ ሆኖ ወደ ኢትዮጵያ የገባ ዕቃ ሚኒስቴሩ በቅድሚያ ሳይፈቅድና ተገቢው

CamScanner

የጉምሩክ ቀረጥ ሳይከፈልበት አይተላለፍም። ሆኖም ተቆጣጣሪውን ባለስልጣን በቅድሚያ በማስፈቀድ ዕቃውን የጉምሩክ ቀረጥ ሳይከፈልበት መልሶ ከሀገር ማስወጣት ወይም ተመሳሳይ የቀረጥ ነፃ መብት ላለው ሰው ማስተላለፍ ይቻላል።

7) ለዚህ የደንቡ ክፍል አፈፃፀም "አላቂ ዕቃ" ማለት ለማዕድን፤ ለነዳጅ እና ለጂኦተርማል ስራዎች የሚያሰፈልግ ኬሚካል፤ ድማሚት እና ሌሎች ሚኒስቴሩ በሚያወጣው መመሪያ የሚዘረዝራቸው ዕቃዎች ናቸው።

8) በዚህ አንቀጽ መሰረት በበላሀብቱ እና በተቆጣጣሪው ባለስልጣን መካከል የሚገቡት ስምምነቶች ወይም የስራ ፕሮግራሞች ከመጽደቃቸው በፊት በጉምሩክ አዋጁ በተደነገገው መሰረት ሚኒስቴሩ አስተያየት ሊሰጥበት ይገባል።

ክፍል ስድስት

የታክስ ማበረታቻዎች አስተዳደር

25. የአፈጻጸም ስምምነት

1) አግባብነት ያለው የኢንቨስትመንት ተቋም በዚህ ደንብ መሰረት የታክስ ማበረታቻ በተፈቀደበት የኢንቨስትመንት መስክ ከሚሰማሩ ባለሀብቶች ጋር የአፈጻጸም ስምምነት ይፈራረማል።

2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሰረት የሚፈረመው የአፈጻጸም ስምምነት የኢንቨስትመንቱን ደረጃ፤ የካፒታል መጠን፤ የሚፈጠረውን የስራ እድል ብዛት፤ የኤክስፖርት ግብ፤ የአገር ውስጥ ጥሬ እቃን የመጠቀም ደረጃ፤ የቴክኖሎጂ ሽግግር እና የመሳሰሉትን የአፈጻጸም መለኪያዎች የሚይዝ እና የሪፖርት አቀራረብ ስርአት የሚዘረጋ ሊሆን ይገባል።

3) የአፈጻጸም ስምምነቱ ግብር ከፋዩ በገባው ግዴታ መሰረት ባይፈጽም መንግስት ማበረታቻውን ቀሪ ማድረግ የሚችል መሆኑን የሚገልጽ መሆን አለበት።

26. በግንባታ ዕቃዎች ላይ ስለሚደረግ ቁጥጥር

1) በዚህ ደንብ መሠረት የግንባታ ዕቃዎችን የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ማበረታቻ ተጠቃሚ ሆኖ ወደ አገር እንዲያስገባ የተፈቀደለት ባለሀብት የግንባታ ዕቃዎቹ ለታለመው ዓላማ የዋሉ መሆኑን የሚያስረዳ የግንባታ ፈቃድ በሰጠው የመንግሥት መሥሪያ ቤት የተረጋገጠ ማስረጃ በየሦስት ወሩ ማቅረብ አለበት።

2) በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (1) የተጠቀሰው ለልዩ የኢኮኖሚ ዞን ግንባታ ተፈፃሚ አይሆንም።

3) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት ከቀረጥ ነጻ ሆነው ወደአገር የሚገቡ የግንባታ እቃዎችን አይነት፤ ሊቀርቡ የሚገባቸውን ማስረጃዎች ዓይነት

CamScanner

እና ለየትኛው አካል ማቅረብ እንዳለበት ሚኒስቴሩ በሚያወጣው በመመሪያ ይወሰናል።

27. የተቆጣጣሪ መስሪያ ቤቶች የወል ተግባርና ኃላፊነት

ተቆጣጣሪ መስሪያ ቤቶች፣

1) ባለሀብቱ የገቢ ግብር ማበረታቻ ተጠቃሚ መሆን እንዲችል ለሚኒስቴሩ የሚከተለውን ማረጋገጫ ይሰጣሉ፣

   ሀ) ባለሀብቱ የንግድ ፈቃድ አውጥቶ እየተንቀሳቀሰ ስለመሆኑ፣

   ለ) ባለሀብቱ ምርት ማምረት ወይም አገልግሎት መስጠት የጀመረበትን ጊዜ፣

2) በዚህ ደንብ መሠረት የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ማበረታቻ የመሆን ማበረታቻ የሚፈቀድለት ባለሀብት ወደ አገር ሊያስገባቸው የሚችሉ ለኢንቨስትመንቱ አስፈላጊ የሆኑ ዕቃዎች ዝርዝር እና ትክክለኛ እና ወቅታዊ ዋጋቸው በሚመለከት ለሚኒስቴሩ የውሳኔ ሀሳብ ያቀርባሉ፣

3) ለኢንቨስትመንት ማበረታቻዎች ብቁ የሚሆኑ የኢንቨስትመንት መስኮች ለመምረጫ የሚያገለግሉ መስፈርቶች በሚዘጋጁበት ጊዜ ይሳተፋሉ፣

4) ማንኛውንም ባለሀብት የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ማበረታቻ ተጠቃሚ ሆኖ ወደ አገር ያስገባውን ዕቃ ዋጋው እና ቀሪ የተደረገውን ቀረጥ መጠን የሚያሳይ ሪፖርት በየሩብ ዓመቱ ለሚኒስቴሩ ያቀርባሉ፣

5) ለባለሀብቱ የተሰጠውን የኢንቨስትመንት ማበረታቻ እና የተገኘውን ጥቅም በተለይም የሥራ ዕድል በመፍጠር፣ የውጭ ምንዛሪ ግኝትን በማሳደግ ረገድ እያንዳንዱ ባለሀብት ለአገሪቱ ያስገኘውን ጥቅም የሚያሳይ ሪፖርት የበጀት ዓመቱ በተጠናቀቀ በሦስት (3) ወር ጊዜ ውስጥ ለሚኒስቴሩ ያቀርባሉ።

28. የኢንቨስትመንት ተቋማት ተግባር እና ኃላፊነት

የዚህ ደንብ አንቀጽ 18 አጠቃላይ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ የኢንቨስትመንት ተቋማት የሚከተሉት ተግባር እና ኃላፊነቶች ይኖራቸዋል፣

1) የኢንቨስትመንት ፈቃድ የሰጧቸው ባለሀብቶች በዚህ ደንብ መሠረት ፣

   ሀ) የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ማበረታቻ የመሆን ማበረታቻ ለማግኘት በተዘረጋው ስርዓት አማካኝነት የሚያቀርቡትን ማመልከቻ ይቀበላሉ፣ የማበረታቻ ጥያቄው አግባብ ካለው ሕግ ጋር የተጣጣመ መሆኑን እና የሚቀርቡ ሰነዶች ትክክለኛነት በመመርመር ያረጋግጣሉ፣ ከድጋፍ ጋር ለውሳኔ ለሚኒስቴሩ ያስተላልፋሉ፣

   ለ) የገቢ ግብር ማበረታቻ ተጠቃሚ ለመሆን በተዘረጋው ስርዓት አማካኝነት የሚያቀርቡትን ማመልከቻ ይቀበላሉ፣ የማበረታቻ

CamScanner

ጥያቄው አግባብነት ካለው ሕግ ጋር የተጣጣመ መሆኑን እና የሚቀርቡ ሰነዶችን ትክክለኛነት በመመርመር ያረጋግጣሉ፣ በዚህ ደንብ አንቀጽ 27 መሰረት ከባለሀብቱ ጋር ተገቢውን የአፈፃፀም ውል በመግባት ከድጋፍ ደብዳቤ ጋር ለውሳኔ ለሚኒስቴሩ ያስተላልፋሉ።

2) አግባብነት ባለው ሕግ እና መመሪያ መሰረት የካፒታል እና የግንባታ ዕቃዎችን እና ተሽከርካሪዎችን የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ማበረታቻ ተጠቃሚ ሆኖ ወደ አገር እንዲያስገባ የተፈቀደለት ባለሀብት ዕቃዎቹን ለታለመላቸው ዓላማ ያዋለ መሆኑን ለመቆጣጠር በመስክ ምልከታ፣ በሪፖርት፣ ተቆጣጣሪ በመመደብ ወይም በሌላ ማናቸውም ዘዴ ተከታታይነት ያለው ክትትል ያካሂዳል፤ በየአመቱም ለሚኒስቴሩ የተጠቃለለ የአፈፃፀም ሪፖርት ይልካል።

3) በዚህ ደንብ አንቀጽ 25 መሰረት ባለሀብቱ በገባው የአፈጻጸም ስምምነት መሰረት የአፈጻጸም መለኪያዎቹ የተሟሉ መሆኑን ማረጋገጥ የሚያስችል የሪፖርት አቀራረብ ስርአት ይዘረጋል።

4) ባለሀብቱ በአፈጻጸም ስምምነቱ በገባው ግዴታ መሰረት የአፈፃፀም ስምምነቱን ሳይፈጽም የቀረ መሆኑን ሲያረጋግጥ የተሰጠው የገቢ ግብር እና የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ማበረታቻ ቀሪ እንዲሆን ለሚኒስቴሩ የውሳኔ ኃሳብ ያቀርባል።

29. የታክሱ ባለስልጣን ተግባር እና ኃላፊነት

የታክሱ ባለስልጣን፣

1) የተፈቀደው የገቢ ግብር ማበረታቻ አግባብነት ካለው ህግ ጋር የተጣጣመ መሆኑን በመመርመር የገቢ ግብር ማበረታቻውን ተፈፃሚ ያደርጋል።

2) የገቢ ግብር ማበረታቻ የተሰጣቸውን ባለሀብቶች ዝርዝር፣ የተሰጣቸውን የማበረታቻ ተፈፃሚ የሚሆንበትን የጊዜ ርዝመት እና የሚያበቃበትን ጊዜ የሚያሳይ መዝገብ ይይዛል፣

3) በዚህ ደንብ መሠረት በተሰጠው የገቢ ግብር ማበረታቻ ምክንያት የታጣውን የገቢ ግብር የሚያሳይ መዝገብ ይይዛል፣

4) ከሌሎች መካከል፣ የገቢ ግብር ማበረታቻ የተሰጣቸውን ባለሀብቶች ዝርዝር፣ የተሰማሩበትን የኢንቨስትመንት መስክ እና ለባለሀብቶች በተሰጠው የገቢ ግብር ማበረታቻ ምክንያት የታጣውን ገቢ የሚያሳይ ሪፖርት የበጀት ዓመቱ በተጠናቀቀ በ2 (ሁለት) ወር ጊዜ ውስጥ ለሚኒስቴሩ ያቀርባል።

30. የጉምሩክ ኮሚሽን ሥልጣንና ተግባር

የጉምሩክ ኮሚሽን፣

CamScanner

1) የተፈቀደው የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ማበረታቻ አግባብነት ካለው ሕግ ጋር የተጣጣመ መሆኑን በመመርመር ዕቃዎች በተሰጠው ማበረታቻ መሰረት ወደ አገር ውስጥ እንዲገቡ ያደርጋል፡፡

2) የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ማበረታቻ የተፈቀደላቸውን ባለሀብቶች ዝርዝር፣ የተሠማሩበትን የኢንቨስትመንት መስክ እና የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ማበረታቻ ተጠቃሚ ሆነው ወደ አገር የገቡትን ዕቃዎች ዋጋ እና የታጣውን ገቢ የሚያሳይ መዝገብ ይይዛል፣

3) ባለሀብቶች የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ማበረታቻ ተጠቃሚ ሆነው ወደ አገር ያስገቧቸው ዕቃዎች ለታለመላቸው ዓላማ የዋሉ መሆኑን ማረጋገጥ የሚያስችል መደበኛ ክትትል እንዲሁም የድህረ ኦዲት ተግባር ያከናውናል፡ ፡

4) ባለሀብቶች በጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ማበረታቻ ወደ አገር ያስገቧቸውን ዕቃዎች ለታለመለት ዓላማ ያላዋሉ መሆኑ በኦዲት ሲረጋገጥ ፀንተው በሚሠራባቸው ሕጎች መሠረት ሕጋዊ እርምጃ ይወስዳል፡፡

5) በዚህ አንቀጽ መሠረት የተከናወኑ ተግባራትን የሚያሳይ የሩብ አመት ሪፖርት የሩብ ዓመቱ በተጠናቀቀ በ30 (ሠላሳ) ቀናት ጊዜ እንዲሁም ዓመታዊ ሪፖርት የበጀት ዓመቱ በተጠናቀቀ በሁለት ወር ጊዜ ውስጥ ለሚኒስቴሩ ያቀርባል፡፡

31. የገንዘብ ሚኒስቴር ተግባርና ኃላፊነት

የገንዘብ ሚኒስቴር፣

1) የዚህን ደንብ ዓላማ ሚያሳካ እና በቂ የኢኮኖሚ ምክንያት መኖሩ ሲያምንበት ማበረታቻ በሚያስፈልገው እና በዚህ ደንብ ከተመላከተው ውጭ በሌሎች የኢንቨስትመንት መስኮች የሚሰማሩ ባለሀብቶች ተገቢውን የኢንቨስትመንት ማበረታቻ እንዲያገኙ በመመሪያ ሊፈቀድ ይችላል፡፡

2) በዚህ ደንብ መሰረት ለማበረታቻ ብቁ ለሆነ ኢንቨስትመንት የተሰጠውን የገቢ ግብር ማበረታቻ ወይም የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ማበረታቻ የሚያስገኝ የኢንቨስትመንት ማበረታቻ ይሰጣል፡፡

3) የኢንቨስትመንት ማበረታቻ ለመስጠት የሚያገለግሉ ተጨማሪ መስፈርቶችን፣ የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ማበረታቻ ተጠቃሚ ሆነው ወደ አገር ሊገቡ ወይም ከአገር ውስጥ ሊገዙ የሚችሉ ዕቃዎችን ዝርዝር፣ የእነዚህ የኢንቨስትመንት ማበረታቻዎች ተጠቃሚ ለመሆን ጥያቄ የሚያቀርቡ ባለሀብቶች ሊያቀርቧቸው የሚገባ ሰነዶችን የሚያሳይ መመሪያ ያወጣል፡፡

4) እያንዳንዱ ተቆጣጣሪ መስሪያ ቤት የኢንቨስትመንት ማበረታቻ ለታለመለት ዓላማ የዋለ መሆኑን በማረጋገጥ ረገድ ያከናወነውን ተግባር በመደበኛ ሁኔታ ይቆጣጠራል፡፡

CamScanner

5) የኢንቨስትመንት ማበረታቻ በመሰጠቱ ምክንያት የታጣውን ገቢ ያጠቃልላል፣ የተጠቃለለውን ሂሣብ እና የኢንቨስትመንት ማበረታቻው በመሰጠቱ ምክንያት የተገኘውን ጥቅም የሚያሳይ ሪፖርት በዓመታዊ የመንግሥት የሂሣብ ሪፖርት ውስጥ በማካተት ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ያቀርባል፣ በየዓመቱ ይህንን ሪፖርት አትሞ ለሕዝብ ይፋ ያደርጋል፡ ፡

6) የተፈቀደውን የኢንቨስትመንት ማበረታቻ መተንተን እና መቆጣጠር የሚያስችል የመረጃ ቋት ያደራጃል፣

7) የተሰጡ የኢንቨስትመንት ማበረታቻዎችን ለመቆጣጠር እና ግልጽ ለማድረግ የሚያስችል በዘርፍ እና በኢንዱስትሪ ደረጃ የሚከተሉትን መረጃዎች ይይዛል፣

ሀ) ለተመዘገቡ ባለሀብቶች የተሰጠውን የኢንቨስትመንት ማበረታቻ፣

ለ) ለቀጣይ የበጀት ዓመት ባለሀብቶች ሊያቀርቡ ይችላሉ ተብሎ የሚገመተውን የኢንቨስትመንት ማበረታቻ ጥያቄ፣

ሐ) በተያዘው የበጀት ዓመት ሊፈቀድ ይችላል ተብሎ በዕቅድ የተያዘውን የኢንቨስትመንት ማበረታቻ፣

መ) ለቀጣይ የበጀት ዓመት ሊፈቀድ ይችላል ተብሎ የታቀደውን የኢንቨስትመንት ማበረታቻ፣

8) የኢንቨስትመንት ማበረታቻ በአገሪቱ ኢኮኖሚ ላይ የሚኖረውን ውጤት ለማወቅ እንዲቻል የተሰጠውን ማበረታቻ እና በማበረታቻው ምክንያት የተገኘውን ጥቅም የሚያሳይ ትንታኔ ያከናውናል፡፡

ክፍል ሰባት

ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

32. የታክስ ማበረታቻን ቀሪ ስለማድረግ

1) የኢንቨስትመንት ፈቃዱ የተሰረዘበት ባለሀብት የወሰደውን የኢንቨስትመንት ማበረታቻ እንዲመልስ ይደረጋል፡፡

2) ያለአግባብ የተወሰዱ የኢንቨስትመንት ማበረታቻዎች የሚመለሱበት ሁኔታ ሚኒስትሩ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል፡፡

33. ሪፖርት የማቅረብ ኃላፊነትን ባለመወጣት ስለሚጣል መቀጫ

1) ማናቸውም የመንግሥት ባለሥልጣን ወይም ሠራተኛ በቂ ምክንያት ሳይኖረው በዚህ ደንብ በተደነገገው መሠረት ስለታክስ ማበረታቻዎች አፈፃፀም ሊያቀርብ የሚገባውን ሪፖርት ወይም መረጃ ያላቀረበ እንደሆነ ፀንተው በሚሠራባቸው ሕጎች መሠረት በወንጀል ወይም በአስተዳደር

CamScanner

የሚኖርበት ተጠያቂነት እንደተጠበቀ ሆኖ እስከ 3 (ሶስት) ወር የሚደርስ ደመወዝ የገንዘብ መቀጫ ይቀጣል።

2) ሚኒስቴሩ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተጣለውን የገንዘብ መቀጫ የመጣልና የመሰብሰብ ሥልጣን ተሰጥቶታል።

34. በወንጀል ተጠያቂ ስለመሆ

ሀ/ የኢንቨስትመንት ማበረታቻ ለማግኘት ኃሰተኛ ሰነዶችን ያቀረበ ባለሀብት እና የሰነዱን ትክክለኛነት ሳያጣራ ያስተላለፈ የተቆጣጣሪ ተቋም ኃላፊ እና ያረጋገጠው ባለሙያ፣

ለ/ ስራ ላይ ለሌለ ፕሮጀክት የኢንቨስትመንት ማበረታቻ እንዲፈቀድ የጠየቀ ባለሃብት፣

ሠ/ የኢንቨስትመንት ማበረታቻውን ለታለመለት ዓላማ መዋሉን በተመለከተ ሀሰተኛ ሪፖርትን ያቀረበ ባለሃብት፣

አግባብ ባላቸው ህጎች መሰረት በወንጀል ተጠያቂ ይሆናል።

35. መመሪያ የማውጣት ሥልጣን

ሚኒስቴሩ ለዚህ ደንብ አፈፃፀም የሚያግዙ መመሪያዎች ሊያወጣ ይችላል።

36. የመሸጋገሪያ ድንጋጌዎች

1. የተሻሩትን የኢንቨስመንት ማበረታቻና ለአገር ውስጥ ባለሀብቶች የተከለሉ የሥራ መስኮች የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር (እንደተሻሻለ) 270/2005 እና የኢንቨስትመንት ማበረታቻ ደንብ ቁጥር (እንደተሻሻለ) 517/2014 መሠረት በማድረግ የተሰጡ ማበረታቻዎች የተሰጠው የታክስ ማበረታቻ ጊዜ እስከሚጠናቀቅ ድረስ ተፈፃሚነታቸው ይቀጥላል።

2. ይህ ማሻሻያ ስራ ላይ ከዋለበት ቀን በፊት የሚኒስትሮች ምክር ቤት ባጸደቃቸው የማዕድን፣ የነዳጅ፣ ጂኦተርማል፣ ባዮ ፊዩል እና የተፈጥሮ ጋዝ ስምምነቶች የተፈቀዱ ከቀረጥ እና ታክስ ነጻ የመሆን መብቶች ተፈጻሚነት ይቀጥላል።

37. የተሻሩና ተፈፃሚነት የማይኖራቸው ሕጎች

1. የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢንቨስትመንት ማበረታቻ ደንብ ቁጥር 517/2014 (እንደተሻሻለ) በዚህ ደንብ ተሽሯል።

2. ከዚህ ደንብ ጋር የሚቃረን ማናቸውም ደንብ፣ መመሪያ ወይም አሠራር በዚህ ደንብ በተደነገጉ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም።

38. ደንቡ የሚፀናበት ቀን

CamScanner

ይህ ደንብ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡
:

አዲስ አበባ ሐምሌ ___ቀን 2018 ዓ/ም

አብይ አህመድ (ዶ/ር)

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ

ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር

CamScanner

ሰንጠረዥ 1

ከልዩ የኢኮኖሚ ዞን ውጪ ለሚደረግ ኢንቨስትመንት የሚሰጥ የ15 በመቶ ቅናሽ የገቢ ግብር መጣኔ ተግባራዊ የሚሆንባቸው የኢንቨስትመንት መስኮች

ተ.ቁ	የኢንቨስትመንት መስክ	በአዲስ አበባና በአዲስ አበባ ዙሪያ ኦሮሚያ ሸግር ልዩ ዞን (በዓመት)	በሌሎች አካባቢዎች (በዓመት)
1.	**የአምራች ኢንዱስትሪ**		
1.1.	የቆዳና ጨርቃ ጨርቅ አምራች ኢንዱስትሪ	4	6
1.2.	የኬሚካልና የኬሚካል ውጤቶች ኢንዱስትሪ	5	6
1.3.	የመሠረታዊ መድኃኒት ምርት እና የመድኃኒት ኢንዱስትሪ	6	8
1.4.	የመሠረታዊ ብረታ ብረት ኢንዱስትሪ (ማሽነሪ ማምረትን ጨምሮ)	5	6
1.5.	ብረት ያልሆኑ የማዕድን ውጤቶች ኢንዱስትሪ	4	6
1.6.	የኮምፒዩተር፣ የኤሌክትሮኒክስ እና የዕይታ ዕቃዎች ኢንዱስትሪ	5	6
1.7.	የኤሌክትሪክ ዕቃዎች ኢንዱስትሪ	3	5
1.8.	የመንገዣ ተሽከርካሪዎች እና ሌሎች የትራንስፖርት መሳሪያዎችን ማምረትና ወይም መገጣጠም	5	6
1.9.	የወረቀት ኢንዱስትሪ	5	6
1.10.	የእንጨት ውጤቶች ኢንዱስትሪ	2	3
1.11.	ፓኬጂንግ	3	5
2.	**ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ልማትና አገልግሎት መስክ**	3	4
3.	**የኤሌክትሪክ ኃይል ማመንጨት፣ ማስተላለፍና ማከፋፈል**	6	8

CamScanner

4.	አግሮ ፕሮሰሲንግ (ወይም ደግሞ ኮሜርሺያል አግሪካልቸር)	5	6

CamScanner

CamScanner

ሰንጠረዥ 2

የካፒታል አላዋንስ የሚፈቀድባቸው የኢንቨስትመንት ዘርፎች እና መጣኔ

የኢንቨስትመንት ዘርፍ	የመጀመሪያ አመት አላዋንስ	ቀጣይ የእርጅና ቅናሽ መጣኔ	ሁኔታዎች
የግብርና ሜካናይዜሽን መሳሪያዎች	በመጀመሪያ አመት የካፒታል ወጪው 50%	በቀሪው የካፒታል ወጪ ላይ በየአመቱ 25%	ተፈጻሚ የሚሆነው ከግብርና ስራ ጋር ለተያያዘ ወጪ ብቻ ነው
ህንጻ- የፋብሪካ፤ የሆቴል ህንጻ፤ የግብርና ምርቶችን ማምረቻ ህንጻ	ለመጀመሪያ አመት የግንባታ ወጪው 50%	በቀሪው የግንባታ ወጪ ላይ በየአመቱ 25%	የተመረጡ የግንባታ እቃዎች መጀመሪያ ጥቅም ላይ በሚውሉበት ጊዜ
ሕንጻ- የትምህርት ቤት ህንጻ፤፤ የንግድ ህንጻ፤ የኢንዱስትሪ ህንጻ፤ ደረቅ ወደብ	የመጀመሪያ አመት አላዋንስ የሌለ ሆኖ በየአመቱ የወጪው 10%	የእርጅና ቅናሽ እስከሚጠናቀቅ ድርስ በየአመቱ የወጪው 10%	ቀጥተኛ የእርጅና ቅናሽ
መሳሪያ-የማምረቻ መሳሪያና መገጣጠምያ፤ የሆስፒታል መገልገያ፤ የተሽከርካሪአውሮፕላንና ፓርት	በመጀመሪያ አመት የካፒታል ወጪው 50%	በቀሪው የካፒታል ወጪ ላይ በየአመቱ 25%	ቅድሚያ የሚሰጣቸው መሳሪያዎች እና መገልገያዎች

CamScanner

CamScanner

ሰንጠረዥ 3- የየጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ማበረታቻ ተጠቃሚ የሚሆኑ የኢንቨስትመንት መስኮች

ተ.ቁ	የኢንቨስትመንት መስክ
1	**1.1 የምግብ ኢንዱስትሪ**
	1.1.1ሥጋና የስጋ ውጤቶች ማቀነባበርና መጠበቅ
	1.1.2ዓሣና የዓሣ ውጤቶችን ማቀነባበር
	1.1.3አትክልትና ፍራፍሬ ማቀነባበርና መጠበቅ
	1.1.4የምግብ ዘይት ማምረት
	1.1.5ወተት ማቀነባበር እና/ወይም የወተት ውጤቶችን ማምረት
	1.1.6የምግብ ማሻሻያ፣ ተጨማሪዎች ወይም ንጥረ ነገሮች ወይም ስታርችና የስታርች ውጤቶችን ማምረት
	1.1.7የእህል ምርት ውጤቶችን ማቀነባበር (ዱቄት ማምረትን ሳይጨምር)
	1.1.8ስኳር ማምረት
	1.1.9ማካሮኒ፣ ፓስታ እና/ ወይም የመሳሰሉ ምግቦችን ማምረት
	1.1.10 አዮዲን የተጨመረበት ጨው ማምረት
	1.1.11 ሰው ሰራሽ ማር ማምረት
	1.1.12 ተቆልቶ የተፈጨ ቡና፣ የሚሟሟ ቡና፣ ሻይ ማምረት
	1.1.13 የእንስሳት መኖ ማቀነባበር
	1.2 የመጠጥ ኢንዱስትሪ
	1.2.1የአልኮል መጠጥ ማምረት
	1.2.2የወይን ጠጅ ማምረቻ
	1.2.3ቢራ እና/ ወይም የቢራ ብቅል ማምረት
	1.2.4የማዕድን ወይም የታሸጉ ሌሎች ውኃዎችን ማምረት
	1.2.5ለስላሳ መጠጥ ማምረት
	1.3 የጨርቃ ጨርቅና የስፌት ውጤቶች ኢንዱስትሪ

CamScanner

ተ.ቁ	የኢንቨስትመንት መስክ
	1.3.1የተለያዩ የጨርቃጨርቅ ጭረቶችን ማዘጋጀት፣ መፍተል፤ መሸመን፣ ማጠናቀቅ እና ወይም ማተም (አልባሳትን ሳይጨምር)
	1.3.2ጣቃ ጨርቅ፣ ክር፣ ድርና ማግ፣ አልባሳትና ሌሎች የጨርቃ ጨርቅ ውጤቶችን በማንጣት፣ በማቅለም፣ በማኮማተር፣ በማፍካት፣ በማጠንከር፣ ወርድንና ቁመትን በመጠበቅ ወይም በማስዋብ ማጠናቀቅ
	1.3.3ከአልባሳት በስተቀር የተዘጋጁ ጨርቃ ጨርቆችን ወይም ሹራብ ወይም ፎጣ ወይም ምንጣፍ ማምረት
	1.3.4የጨርቃ ጨርቅ አልባሳትን (የስፖርት አልባሳትን ጨምሮ) ወይም ተጓዳኝ አካላትን (አክሰሰሪስ) ማምረት
	1.4 የቆዳና የቆዳ ውጤቶች ኢንዱስትሪ
	1.4.1ቆዳና ሌጦ ማለስለስና ማጠናቀቅ (ካለቀለት ደረጃ በታች ቆዳና ሌጦ ማልፋትን አይጨምርም)
	1.4.2ካለቀለት ደረጃ በታች ቆዳና ሌጦ ማልፋት
	1.4.3የቆዳ ውጤቶች እና/ወይም ተጓዳኝ አካላትን (አክሰሰሪስ) ማምረት
	1.4.4የቆዳ ወይም የቆዳ ምትክ ጫማ ማምረት
	1.5 የእንጨት ውጤቶች ኢንዱስትሪ
	1.5.1የእንጨት ውጤቶችን (እንጨት መሰንጠቅን፣ ጣውላ ማምረትን እና ቀድመው የተዘጋጁ የእንጨት ውጤቶችን መገጣጠምን ሳይጨምር) ማምረት
	1.6 የወረቀትና የወረቀት ውጤቶች ኢንዱስትሪ
	1.6.1ፐልፕ እና/ ወይም ወረቀት ማምረት
	1.6.2የወረቀት ውጤቶችን ማምረት
	1.7 የማተሚያ ኢንዱስትሪ
	1.8 የኬሚካልና የኬሚካል ውጤቶች ኢንዱስትሪ
	1.8.1መሠረታዊ ኬሚካሎችን (ኢታኖልን እና/ ወይም ሰው ሰራሽ ጭረቶችን ጨምሮ)፤ እና/ወይም ሃይድሮጂን አና አሞኒያ ማምረት
	1.8.2ማዳበሪያ እና /ወይም የናይትሮጅን ውህዶችን ማምረት
	1.8.3መሰረታዊ (የመጀመሪያ ደረጃ) ፕላስቲኮችን እና/ወይም ሲንቴቲክ (ሰዉ ሰራሽ) ጎማ ጥሬ ዕቃዎችንና ጎማ ውጤቶችን ማምረት

CamScanner

ተ.ቁ	የኢንቨስትመንት መስክ
	1.8.4ጸረ- ተባይና የግብርና ኬሚካሎችን ማምረት
	1.8.5ቀለም፣ ቫርኒሽ እና ተመሳሳይ ምርቶች፣ማጣበቂያ እና/ወይም መሰረታዊ ያልሆኑ ኬሚካሎችን ማምረት
	1.8.6የንፅህናና የኮስሞቲክስ ዕቃዎች እና ግብዓቶች መፈብረክ
	1.9 የመሠረታዊ መድኃኒት ምርት እና የመድኃኒት ኢንዱስትሪ
	1.9.1ለመድኃኒት ግብዓትነት የሚውሉ መሠረታዊ የመድኃኒት ውጤቶችን ማምረት
	1.9.2ለሰው አገልግሎት የሚውል መድኃኒት ማምረት(ክትባት ማምረትን ጨምሮ)
	1.9.3ለእንሰሳት አገልግሎት የሚውል መድኃኒት ማምረት(ክትባት ማምረትን ጨምሮ)
	1.9.4ከመድኃኒት ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ያላቸውን የማሸጊያ ምርቶች ማምረት
	1.9.5የመድኃኒት ማሸግ ስራዎች
	1.10የፕላስቲክ ውጤቶች ኢንዱስትሪ
	1.10.1 ፌስታልን ሳይጨምር የፕላስቲክ ውጤቶችን ማምረት
	1.11ብረት ያልሆኑ የማዕድን ውጤቶች ኢንዱስትሪ
	1.11.1 መስተዋት እና/ወይም የመስታወት ወይም የሴራሚክ ውጤቶችን ማምረት
	1.11.2 ሲሚንቶ ማምረት
	1.11.3 የሸክላና የሲሚንቶ ውጤቶች ማምረት
	1.11.4 የካባ ድንጋዮችን ማውጣት ሳይጨምር የድንጋይ ውጤቶችን፣ ዕብነ በረድ እና ግራናይት የኖራ ድንጋይ መቁረጥ፣ ቅርፅ ማውጣት እና ማጠናቀቅ
	1.11.5 ኖራ ፣ ጂሶ እና /ወይም የመሳሰሉ መለሰኛዎችን ማምረት
	1.12የመሠረታዊ ብረታ ብረት ኢንዱስትሪ /የማዕድን ማውጣትን ሳይጨምር/
	1.12.1 ብረት ፣የአረብ ብረት እና የብረት ማዕድናት ውጤቶችን መፈብረክ
	1.12.2 መሠረታዊ የከበሩና የብረት ይዘት የሌላቸው ብረታ ብረቶችን ማምረት
	1.12.3 ከብረት እና ማግኔታዊ ያልሆኑ ብረታ ብረቶች ማቅለጥ /ማድለብና የተለያዩ ቅርፆችን ማውጣት
	1.13ለስትራክቸር የሚያገለግሉ የብረታ ብረት ውጤቶች ኢንዱስትሪ
	1.13.1 የማዋቀሪያ እና የተለያዩ የብረታ ብረት ውጤቶችን ማምረት (የቤት ክዳን ቆርቆሮንና ሚስማርን ሳይጨምር)

CamScanner

ተ.ቁ	የኢንቨስትመንት መስክ
	1.14 የኮምፒዩተር፣ የኤሌክትሮኒክስ እና የዕይታ ዕቃዎች ኢንዱስትሪ
	1.14.1 ኮምፒዩተር እና ተንዳኝ ዕቃዎችን እና/ወይም የኤሌክትሮኒክስ አካሎችንና ሰሌዳዎችን ማምረት
	1.14.2 የመገናኛ መሣሪያዎችን ወይም የፍጆታ ኤሌክትሮኒክስ /ቴሌቪዥን፣ዲቪዲ፣ ሬዲዮ እና የመሳሰሉት/ ዕቃዎችን ማምረት
	1.14.3 የመለኪያ፤ የመፈተሻ፤ የመቃኛ፤ የመቆጠጠሪያ መሳሪያዎችን ወይም ሰአት ማምረት
	1.14.4 የህክምና መሳሪያዎችን ወይም አቅርቦቶችን ማምረት
	1.14.5 የህክምና መሳሪያዎችን መገጣጠም
	1.14.6 የዕይታ ወይም የፎቶ ማንሻ ወይም መግነጢሳዊ እና የዕይታ ሚዲያ ዕቃዎችን ማምረት
	1.15 የኤሌክትሪክ ዕቃዎች ኢንዱስትሪ
	የኤሌክትሪክ ዕቃዎችን ማምረት
	1.16 የማምረቻ/አገልግሎት መስጫ መሣሪያዎችና ዕቃዎች ኢንዱስትሪ
	1.16.1 ለሁለገብ አገልግሎት ሥራ የሚያገለግሉ መሣሪያዎች ማምረት
	1.16.2 ለልዩ አገልግሎት የሚውሉ መሣሪያዎችን ማምረት
	1.17 የመጓጓዣ ተሽከርካሪዎች እና ሌሎች የትራንስፖርት መሳሪያዎችን ማምረት
	1.17.1 የሞተር ተሽከርካሪዎን (መኪና) ማምረት
	1.17.2 የመኪና አካላትን፣ተጎታችን እና/ ወይም ከፊል ተጎታችን ወይም መለዋወጫዎችን እና ተንዳኝ አካላትን ማምረት
	1.17.3 በባቡር እና በትራም መንገድ የሚሄዱ ሎኮሞቲቮችን እንዲሁም ዘዋሪ እግር ያላቸውን ተሽከርካሪዎችን እና ጋሪዎችን ማምረት
	1.17.4 የሞተር ብስክሌቶችን፣ ብስክሌቶችን እና ባለሶስት እግር ተሽከርካሪዎችን መፈብረክ

CamScanner

ተ.ቁ	የኢንቨስትመንት መስክ
	1.17.5 ጀልባዎችን መገንባት
	1.18 የቤትና የቢሮ ዕቃዎች (ከሴራሚክ የሚሰሩትን ሳይጨምር) ማምረት
	1.19 የእደጥበብ፣ የገፀበረከት ዕቃዎች፣ አርቲፊሻል ጌጣጌጥ፣የሙዚቃ እና የስፖርትዕቃዎችን ማምረት
	1.20 ከግብርና ጋር የተቀናጀ የማምረቻ ኢንዱስትሪ
	1.21 የኢንዱስትሪ ፓርክ፤ የኢንፎርሜሽን ኮሚዩኒኬሽን ቴክኖሎጂ ፓርክን ጨምሮ፤ ማልማት እና የማከራየት ስራዎች
	1.22. ማሸጊያ እና ሌብሊንግ ማምረት
	1.23. ሰንደል ማምረት
	1.24. አውሮፕላን ማምረት
	1.25. የአውሮፕላን አካላት ማምረት
	1.26. ድሮን እና የእነዚህን አካላት ማምረት
	1.27. የፈርነስ ዘይት ማምረት
2	2. ግብርና
	2.1 የእርሻ ልማት
	2.1.1 የዓመታዊ ሰብሎች ልማት
	2.1.1.1 የብርዕና የአገዳ ሰብሎች ወይም የሾንኮራ ማልማት
	2.1.1.2 የቅባት እህሎች ማልማት
	2.1.1.3 የጥራጥሬ እህሎች ማልማት
	2.1.1.4 አትክልት፣ ፍራፍሬ፣ እጽዋት እንዲሁም የተረጋገጠ ምርጥ ዘር ማምረት
	2.1.1.5 የጭረት ሰብሎችን ማምረት እና ማዘጋጀት

CamScanner

ተ.ቁ	የኢንቨስትመንት መስክ
	2.1.1.6 የእንሰሳት መኖ ማልማት፣ ለመድኃኒትነት፣ ለሽቶ፣ ለቅመምነት እና ለመሳሰሉት የሚሆኑ ሰብሎችን ማልማት
	2.1.2የመካከለኛ ጊዜ ቋሚ ተክሎች ማልማት
	2.1.2.1 አበባ ማልማት
	2.1.2.2 በርበሬና ቅመማ-ቅመም ማልማት
	2.1.3ቋሚ ተክሎች ልማት
	2.1.3.1 ቡና እና/ወይም ሻይ ቅጠል ማልማት
	2.1.3፣2 የጎማ ዛፍ፣ ጃትሮፋ እና ወይም ፖልም ልማት
	2.2 የእንሰሳት ሀብት ልማት
	2.2.1የቤት እንሰሳት እና ወይም የዱር እንስሳት እርባታ እና ተዋፅኦ ልማት (ማደለብን ሣይጨምር)
	2.2.2የዶሮ እና ወይም አዕዋፋት እርባታእና ተዋፅኦ ልማት
	2.2.3ንብ ማነብ/ማር ማምረት
	2.2.4የሐር ትል ማልማት
	2.2.5በሰው ሰራሽ ኩሬ የባህር እንስሳት/አሳ ማምረት
	2.3 የተጣመረ ግብርና /የእርሻና እንስሳት/ ልማት
	2.4 ደን ማልማት እና ተዛማጅ ስራዎች
	2.5. ችግኝ ማባዛት እና ማምረትን ጨምሮ ቲሹ ካልቸር እና የዘር ማባዛት
	2.6. ቡና ማጠብ፤ መቀሸር፤ ለኤክስፖርት ማዘጋጀት፤ እና መቁላት
	2.7. የተፈጥሮ ማር / ሰም ማቀነባበር/ ማምረት

CamScanner

ተ.ቁ	የኢንቨስትመንት መስክ
3	**የመረጃና መገናኛ ቴክኖሎጂ ልማት መስኮች** 1. የሶፍትዌር ልማት፤ 2. የዳታ ማዕከል እና ክላውድ አገልግሎት፤ 3. ቢዝነስ አውትሶርሲንግ ፕሮሰስ፤ 4. የስታርታፕ ልማት አገልግሎት፤ 5. የምርምር፣ ፈጠራ እና የማበልጸግ ወይም የማልማት ስራ፤
	6. የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ አገልግሎት፤
	7. በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ አስቻይነት የሚከናወኑ ሌሎች አገልግሎቶች
4	**የኤሌክትሪክ ኃይል ማመንጨት፣ ማስተላለፍና ማሰራጨት**
	4.1 የኤሌክትሪክ ኃይል ማመንጨት
	4.2 የኤሌክትሪክ ኃይል ማስተላለፍ፣ ማከፋፈል
5	**ሆቴልና ቱሪዝም**
	5.1 የኮከብ ደረጃ ያለው ሆቴል /ሪዞርት ሆቴልን ጨምሮ/፣ ሞቴል፣ሎጅ
	5.2 የኮከብ ደረጃ ያለው ሬስቶራንት
	5.3 የአስጎብኚነት አገልግሎት
6	**የኮንስትራክሽን ሥራ ተቋራጭነት**
	6.1.1ኮንስትራክሽን ሥራ ተቋራጭነት
	6.1.2የውኃ ጉድጓድ ቁፋሮ
	6.1.3የማዕድን፤ የነዳጅ እና የጂኦተርማል ቁፋሮ
7	**የትምህርት እና ስልጠና** 7.1 የሁለተኛ ደረጃና ከፍተኛ ትምህርት 7.2 የመዋዕለ ህፃናት፣ የአንደኛ ደረጃና መለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ 7.3 የቴክኒክና ሙያ ስልጠና (ስፖርትና ጨምሮ) አገልግሎት

CamScanner

ተ.ቁ	የኢንቨስትመንት መስክ
8	**የጤና አገልግሎት** 8.1 ቴሪሸሪ የልዩ ሆስፒታል አገልግሎት (ዝርዝሩ ሚኒስቴሩ በሚያወጣው መመሪያ የሚወሰን)
	8.2 የሆስፒታል አገልግሎት 8.3 የምርመራ ማዕከል አገልግሎት 8.4 የክሊኒክ አገልግሎት
9	**የአርኪቴክቸር እና የኢንጂነሪንግ ሥራዎች፣ የቴክኒክ ምርመራና ትንተና**
	9.1 የአርኪቴክቸር እና የኢንጂነሪንግ ሥራዎች፣ እና ተዛማጅ የቴክኒክ ማማከር አገልግሎት 9.2 የቴክኒክ ምርመራ እና ትንተና 9.3 የጂኦፊዚክስ እና የላቦራቶሪ አገልግሎት
10	የሎጂስቲክስ አገልግሎት 10.1 የቀዝቃዛ መጋዘን አገልግሎት 10.2 የብትን ጭነት (ሳይሎ) መጋዘን አገልግሎት
	10.3 የደረቅ ወደብ አገልግሎት
11	**ተሽከርካሪን የማይጨምር የካፒታል ዕቃዎች ኪራይ**
12	የገቢ ንግድ ቡታ ጋዝ ወይም ቢትመን ማስመጣት
13	**የጅምላ ንግድ** ነዳጅና የነዳጅ ምርቶችን ማቅረብ እና የራስን ምርት በጅምላ መሸጥ
14	**ልዩ የኢኮኖሚ ዞን**
	14.1. የልዩ ኢኮኖሚ ዞን አልሚ
	14.2. የልዩ ኤኮኖሚ ዞን ንኡስ አልሚ
	14.3. የልዩ ኢኮኖሚ ዞን አስተዳዳሪ
	14.4. የልዩ ኤኮኖሚ ዞን ድርጅት
15.	**ሌሎች አገልግሎቶች**
	15.1. በአውሮፕላን ጸረ ተባይ መርጨት
	15.2. በአነስተኛ አውሮፕላን የትራንስፖርት አገልግሎት መስጠት

CamScanner

ተ.ቁ	የኢንቨስትመንት መስክ
	15.3. የፈሳሽ ቆሻሻ ማጣሪያ እና ማሰወገጃ አገልግሎት
	15.4. የውሃ ላይ ጨዋታ እና የማዝናናት አገልግሎት
	15.5. ቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎት
	15.6. ክሪፕቶ ከረንሲ ማይኒንግ

CamScanner